**ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት**
**የቤት ስራ ፖሊሲ**

1. በኦንላይን መድረክ የቤት ስራ:
   a. የቤት ስራ ኦንላይን ከተሰጠ በተሰጠበት ቀን ክፍል ውስጥ መሰራት/ውይይት መደረግ አለበት። የኦንላይን መድረክ የቤት ስራ መስራትን እና አሰባሰብን በሚያሳልጥ መልኩ መዘጋጀት አለበት፤ በአስተማሪ እና ተማሪ መካከል የሚኖረውን ንግግር በሚተካ/በሚቀይር መልኩ መሆን የለበትም። ለምሳሌ አስተማሪ ኦንላይን የቤት ስራ ከሰጠ የጊዜ ገደብን ባሻገር እና ክፍል ውስጥ ለተማሪዎች ሳይናገር የተሰጠውን የቤት ስራ እንዲሰራ መጠበቅ የለበትም።
   b. ኦንላይን የሚሰጡ የቤት ስራዎች በሙሉ ኦንላይን መሰጠታቸው የተነገረበት የትምህርት ቀን እስኪያልቅ ድረስ ኦንላይን መዘጋት አለባቸው፤ ካልሆነ ተማሪዎች የቤት ስራውን በሚቀጥለው ቀን ሰርተው እንዲያመጡ አይጠበቅም። ለምሳሌ አስተማሪው የቤት ስራውን ማክሰኞ ማታ በ 5:00pm ኦንላይን ቢሰጥ የቤት ስራው ተሰርቶ መጠናቀቅ ያለበት እስከ ሀሙስ ድረስ ነው።
   c. ኦንላይን የቤት ስራ መስጠት ማለት ለቤት ስራው የሚያስፈልጉ ጽሁፎችን ሁሉ አብሮ ማዘጋጀት ማለት ነው። ለምሳሌ አስተማሪ ክፍል ውስጥ የጥያቄዎች ስብስብ ቢናገር እና የጥያቄዎቹን ዝርዝር በኋላ ኦንላይን እንደሚሰጥ ቢናገር የጥያቄዎቹ ዝርዝር ኦንላይን እስከሚሰጥ ድረስ የቤትስራው እንደተሰጠ አይቆጠርም።

2. በት/ቤት እረፍት ወቅት የቤት ስራ የሚሰጡ አስተማሪዎች የቤት ስራው እንዲሰራ ከእረፍት ጊዜው በፊት ወይም በኋላ በቂ ጊዜ መስጠት አለባቸው። ይህ የሚተገበረው የሚከተሉት እረፍቶች ላይ ነው: የታንክስጊቪንግ እረፍት፣ ዊንተር እረፍት፣ ፌብሩዋሪ እረፍት እና አፕሪል እረፍት።
   a. ከእረፍት በኋላ ባሉት የመጀመሪያዎቹ ሁለት የትምህርት ቀናት መሰራት ያለበት የቤት ስራ ከሶስት የትምህርት ቀናት በፊት መሰጠት አለበት። ለምሳሌ እረፍቱ ከአርብ እስከ ሰኞ ከሆነ ከእረፍቱ በኋላ ባለው ሰኞ መሰራት ያለበት የቤት ስራ መሰጠት ያለበት ከእረፍቱ በፊት ባለው እሮብ ነው። እንዲሁም ከእረፍቱ በኋላ ባለው ማክሰኞ መሰራት ያለበት የቤት ስራ መስጠት ያለበት ከእረፍቱ በፊት ባለው ሀሙስ ነው።
   b. አስተማሪ ከእረፍት በፊት ባለው ሀሙስ የቤት ስራ መስጠት እና ከእረፍት በፊት አርብ እንዲሰራ መጠየቅ ይችላል እንዲሁም አስተማሪ ከእረፍት በኋላ ባለው ሰኞ የቤት ስራ መስጠት ይችላል፣ በየትኛውም ቀን መሰራት ቢኖርበትም።
   c. ከእረፍት በኋላ ባሉ ሁለት ቀናት ውስጥ አስተማሪዎች ፈተና መስጠት አይችሉም።
   d. የአንድ ሴሚስተር AP ትምህርቶች ይህ ደንብ አይመለከታቸውም።

3. አስተማሪዎች በተማሪዎች የሚከበሩ ሀይማኖታዊ በአላትን ከግንዛቤ በማስገባት የት/ቤት እረፍት ቢሆንምለሁሉም ተማሪዎች ፕሮጀክቶችን በመስጠት፣ በመፈተን እና በበቂ ጊዜ የቤት ስራ በመስጠት ፍትሀዊነትን ያረጋግጣሉ።
   a. ክፍሉ ውስጥ ያሉ በርካታ ተማሪዎች በአሉን የሚያከብሩት ከሆነ የቤት ስራ መሰጠት ያለበት ከበአሉ አንድ ቀና በላይ ቀደም ብሎ መሆን አለበት፤ የቤት ስራውን መስሪያ እና/ወይም መመለሻ ቀን ከበአሉ ከአንድ ቀና በላይ በኋላ መሆን አለበት። ለፕሮጀክቶች እና ፈተናዎች ተመሳሳይ ፖሊሲ ይተገበራል።
   b. በአሉንየሚያከብሩትክፍሉውስጥያሉአነስተኛተማሪዎችከሆኑአማራጭየቤትስራእንዲዘጋጅወይምየመስሪያጊዜውእንዲራዘምከአስተማሪውጋርመነጋገርይችላሉ፤ ይህበመሆኑከቤትስራውላይየሚቀነስውጤትአይኖርም። ወላጆች አስተማሪዎችን በማነጋገር መፈተኛ ቦታዎችን ማዘጋጀት ይችላሉ።

4. በበረዶ ቀናት የቤት ስራ አይሰጥም እንዲሁም አይሰበሰብም። ሆኖም ይህ ደንብ የረዥም ጊዜ ከባድ የአየር ጸባይ በሚያጋጥምበት ወቅት የት/ቤት ዋና ተቆጣጣሪዎች "ብሊዛርድ ባግስ (መደበኛ ትምህርት ከቤት መከታተል)" እንዲጠቀም ከማጽደቅ እንዲከለክል ተደርጎ አይተረጎምም። አስተማሪ ከበረዶ ቀን በፊት የቤት ስራ ኦንላይን ከሰጠ የቤት ስራው መግባት ያለበት ተማሪዎች ት/ቤት ሲገቡ ነው።

5. ሁሉም የቤት ስራ ተማሪዎች ት/ቤት በሚገቡበት ወቅት መግባት አለበት። አስተማሪ የቤት ስራን ማስገቢያ የጊዜ ገደብ ማራዘም ከፈለገ አዲሱ የጊዜ ገደብ ቀጣዩ የትምህርት ቀን መሆን አለበት።

6. ተጨማሪ ክሬዲት የሚያስገኙ የቤት ስራዎች ት/ቤት ውስጥ ተጨማሪ ጊዜ ማሳለፍን አይጠይቅም።
    a. ተማሪዎች ለተጨማሪ ክሬዲት ከሚማሩበት የትምህርት ሰአት ውጪ አስተማሪዎች ስብሰባ ማድረግ አይችሉም።
    b. እንዲሁም ተማሪዎች ለተጨማሪ ክሬዲት ስጦታ ወይም የመማሪያ ክፍል አቅርቦት እንዲያመጡ አስተማሪዎች መጠየቅ የለባቸውም።

7. የቤት ስራዎች ከተማሪ መደበኛ የት/ቤት አቅርቦት በላይ ሊፈጅ አይገባውም፤ ለችግረኛ ተማሪዎች የገንዘብ እርዳታ ከሌለ በስተቀር።

8. ተማሪዎች ትምህርት ከሚጀመርበት ጊዜ በኋላ የመስክ ጉዞ ባለመሄዳቸው አይቀጡም እንዲሁም ቀሪዎቹ ተማሪዎች የመስክ ጉዞ በሚሄዱበት ወቅት በትምህርት ወቅት ሊያጠናቅቁት ከሚችሉት በላይ ተጨማሪ ስራ እንዲሰሩ ሊጠየቁ አይችሉም። የመስክ ጉዞ ለመሄድ ክሬዲት የሚሰጥ ከሆነ ለማጠናቀቅ ከትምህርት ክፍለ ጊዜ በላይ የማይፈጅ ለመስክ ጉዞው ተሞክሮ መጋቢ የሆነ ተመጣጣኝ የቤት ስራ ይሰጣል።

9. በፈተና ወቅት ከተሰጠ አስተማሪዎች በተመደበው ቀን የእሩብ አመት ፈተና መስጠት አለባቸው። ፈተናው የሚሰጠው ለበርካታ ቀናት ከሆነ ከሁለቱ ዋና የፈተና ቀናት አንዱ እንዲካተቱ አድርጎ አስተማሪው ፕሮግራም ማውጣት አለበት። አስተማሪዎች የእሩብ አመት ፈተናቸውን ከፈተናው ሳምንት በፊት እንዲሰጡ ከመምሪያ አስተባባሪዎቻቸው ጋር መስራት ይችላሉ።

10. ተማሪ በተመደበለት ወቅት የቤት ስራ ለመጨረስ ካልቻለ መጀመሪያ ስለጉዳዩ ከአስተማሪው ጋር መነጋገር አለበት። ጉዳዩን መፍታት ካልተቻለ ተማሪው ተጨማሪ ድጋፍ ለማግኘት የመሪ አማካሪውን፣ ልዩ የትምህርት ተወካይ ወይም ዲን ማነጋገር አለበት።

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ መምህራን ከዚህ ፖሊሲ ጋር የሚጣጣሙ የቤት ስራዎችን በተመለከተ ትምህርት ተኮር ደንቦችን ሊያሰራጭ ይችላል።